




# ለውለታህ ክብር!





(ለድምጻዊ ጥላሁን ገሠሠ መታሰቢያ)

የኪነት ዓምድ የበኩር ልጅ - የመድረኩ አብሪ ፀዳል፣
የሰገነት ባለማዕረግ - ግርማ-ሞገስ ኮከብ አምሳል፣
የሙዚቃው ዓለም ንጉሥ - የቅላፄው ባለዙፋን፣
ላዲስ ትውልድ አርአያ  ባለዝና የኢትዮጵያችን፣
በተፈጥሮ ሕይወት ጥሪ - ብትለይም ከዚህች ዓለም፣
ለጀግንነት፣ ለውለታህ - ክብር ይሁን ለዘልዓለም!

ውርሰ-ያሬድ መንፈስ ዜማ - ጥንተ-ሊቁ ማኅሌታይ፣
በሰልስቱ ተምሳሌት - ግዕዝ፣ ዕዝል፣ አራራይ፣
የዘመናዊ ሙዚቃችን - ዕፁብ፣ድንቅ ኮከብ ግርማ፣
ባለረቂቅ ቅላፄ - መረዋ ድምጽ አበ-ዜማ፤
በ«ክብር ዘብ» ኦርኬስትራ - አጀብ ድምቀት፣
ስንቱን ወጥተህ. . . ወረድክበት. . .፤

በባቲ ለዛ ውበት - በትዝታ ቅኝት ዜማ፣
አፍስልን በረከቱን - መንፈሳችን አይጠማ፤
በ«አልቻልኩም..» ምሬት ዜማህ - የትግል ወኔን አጎናጽፈን፣
በ«ሰዎቹ ምን ይላሉ..» ጥቂት ይሉኝታን አስተምረን፣
ከበቃም በቃ ብለህ - «እችክ፣ እችክ፣ እችክ..» በለን፤
ያለፍነውን እንድናልም - እንድንቆዝም በሰመመን፣
በሃሳብ ጉዞ ትዝታ - በ«የጥንቱ ትዝ አለኝ..» ውሰድና መልሰን፤
በ«እኔ ልሁን እንጂ...» ዜማህ - በ«አንቺን ክፉ አይንካሽ..» . .
ራስን መውቀስ አስለምደን፤
በ«ዋይ! ዋይ! ሲሉ..» ጩኸት - በሰቆቃ ጥሪ ድምጸት፣
ልጉም አፋችንን ከፍተህ - አንቃን ከተኛንበት፤

.. «..ሃርካ ፉኔ ያ ኢሜቴ..»፣ «አካም ነጉማ ፈዩማ..»
ፍቅር ሰላም ለተጠማ -  ለንጹህ ልብ መሳጭ ዜማ፤
«ኢሾ፣ኢሾ፣ ኢሾ..» በለን - በኦሮምኛ አስጨፍረን፣
ባሳብ ምናብ እንዋኝበት - ፍቅርን አይተህ አሳየን፤
የአንድነት የፍቅር ቋንቋ
ኢትዮጵያዊነት ሙዚቃ!
ኑርልን እስከዘላለም!
በድምጽህ ነጎድጓድ ዓለም!












ስንጨነቅ፣ ስንገፋ፣ - ስንረገጥ ስንገዛ፣
ድምጻችንን አስተጋባ - መጽናኛችን ሁነን ቤዛ፤
ስንራብ ስንቸገር - ኑሮ ሕይወት ስንጠላ፣
አብስልን እምባችንን - ጥላ ሁነን ከለላ፤
በትዝታ ፍቅር አዝለህ - «ሩቅ ምስራቅ..» አንጉዘህ..፣
በ«ጃፓኗን ወድጄ...» ካድማስ ወዲያ ሕይወት ቃኝተህ..፣
«ወገን አለኝ፣ ሀገር አለኝ..» «ከሰው ወዲያ በምድር..» ብለህ፣
ማኅበራዊ ሕይወት-አልባ - እንዳንሆን ገስጽ መክረህ፤

በ«እኔ እስክሞት ድረስ..» በ«እይዋት ስትናፍቀኝ..»
ጊዜ-ዘመን እማይሽረው - ዕንቁ ድምጽህ ባየር ይናኝ!
ተንጎራደድ በመድረኩ - በቅላፄህ አስደምመን፣
የሙዚቃው ክቡር ንጉሥ - አቦ! ሁንበትና ሁነን!
ዕድለኞች ነን በብዙ - ባንተ ባለሃብትነታችን፣
በሙዚቃ ውበት ቋንቋ - ትረካለች ነፍሳችን፤
ህያው ታሪክ ባለዘመን - ግብርህ ሥምህ እሚያስመካ፣
ካሳ፣ ጥላ-ከለላችን - የኢትዮጵያችን ታላቅ ዋርካ!

ፍቅር ነው ዘወትር ሃብትህ፤ መድረክ ናት ቪላ ቤትህ፤
ጸጋ ምስጢር ሕይወትህ፣ ሕዝብ ነው ወዳጅ ዘመድህ፤
ሁሌም እምትምልባት፣ ኢትዮጵያ ናት ክብርት እናትህ፤
አንተ ጀግና - ብላቴና፣ አልፈህ ኖረህ በፈተና፣
በኃያል ፍቅር ስትሰግድላት፣ በክብር ሥሟን ስትጠራት፣
ሳታገግም ደክማ ገና - ከህመሟ ሳትጸና፣
እናስ ምነው ጨከንክባት፣ ኢትዮጵያንስ ለማን ተውካት?!
ምኞት ፍቅርህን ግለጽላት፣
«ያንቿው እኮ ነው አምሳሉ..» በላት፡፡

. . .

..ዕድሜ ሙሉ ያዜምክለት - ያ! ሽለቆ .. ያ! ተራራ፣
ለምለም ምድር ክቡር ገላ.. የናት ሀገር ውብ ባንዲራ፣
በቅላፄህ ውበት ዓለም - የቀረጽከው የሕዝብ ፍቅር፣
ከሩ--ቅ አገር ስቦ ወስዶ - የሱነትክን ሊያስመሰክር፣
ያገር አፈር አድባር ጠራህ፣
ለትንሣኤው ሕይወት በቃህ፣
«ክቡር ሞቱ ለሰማዕት»!
ለሙዚቃው ሕያው አባት!
በፈጸምከው ህያው ተግባር - ለእናት ሀገር ልዩ ፍቅር፣
ትውልድ ሁሌም ያስብሃል - ለውለታህ ታላቅ ክብር!!

ጌታቸው አበራ
ሚያዚያ ፪ ሺ ፩ ዓ/ም
(አፕሪል 2009)